# ኢትዮጵያዊነት እንደዋዛ!

("የሀበሻ ጀብዱ" እና "የተደበቀዉ ማስታወሻ" መጻሕፍት ላይ የተደረገ ልዩ ዳሰሳ)

ከመኮንን አሻግሬ (ቨርጂኒያ አሜሪካ)

ስለሀገራችን ፖለቲካ ሳስብ ቀድሞ ወደአእምሮዬ የሚመጣዉ ኢትዮጵያዊነትና እንደሀገር የመቀጠል ሁኔታ ነዉ። የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ የዲሞክራሲ አለመኖር፣ የመልካም አስተዳደር ዕጦት፣ ሥር የሰደደ ሙስና፣ ወያኔ መራሽ ግለሰባዊና ተቋማዊ ዝርፊያ፣ ዘረኝነት፣ ግድያ፣ አፈና ... እጅግ ብዙ ነጥቦችን በማንሣት ስለጥልቀታቸዉና ስለስፋታቸዉ ማዉራት ይችላል። ሆኖም ግን በየቀኑ የምንሰማዉና የምናየዉ በመሆኑ ይህንን መድገም "ለቀባሪ ዐረዱት" እንደሚባለዉ ዐይነት ከመሆን ባሻገር የሚፈይደዉ ነገር ያለ አይመስለኝም።

መንግሥት በሰላማዊ መንገድ ሕዝብን የማስተዳደር ዐቅሙን ሙሉ ለሙሉ በማጣቱ እያዘመመ እንደሆነ በግልጽ የሚታይ ነዉ። የሕዝቡ አልገዛም ባይነት በየጊዜዉ እየሰፋና እየጎለበተ መጥቷል። ከዚህ በኋላ በመንግሥት የሚወሰድ ማናቸዉም የማባበያ ዕርምጃ ወይም የተስፋ ቃል የሕዝቡን ልብ ለማለዘብ ጉልበት አይኖራቸዉም።

ወያኔ/ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ወደቀ እንበል። ቀጣዩ መንግሥት ምን መምሰል አለበት? ሥርዓቱ የተከላቸዉ ችግሮችንና ቁርሾዎችን ተረካቢዉ መንግሥት እንዴት ያስተናግዳቸዋል? በሕዝብ መካከል እንዴት መተማመን መፍጠር ይቻላል ... ወዘተ የሚሉና ሥርዓቱ እንዴት ይወገዳል ከሚለዉ ባልተናነሰ ሊያሳስቡና ሊያስጨንቁ የሚገባቸዉ ነገሮች መነሣታቸዉ አይቀርም። መቼም ወያኔ/ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ ወለድ የሆኑ ዉስብስብ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን የተገነዘበ ሰዉ "እሱን ጊዜ ይፈታዋል" በሚል ቾል እንደማይል ዕሙን ነዉ።

ሥርዓቱ ካስከተላቸዉ ጠንቆች ዉስጥ ምናልባት ዋና ይሆናል ብዬ የማስበዉ የብሔራዊ ስሜት መጥፋት ይመስለኛል። በዛሬ ጊዜ ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ በጎሣ መሰባሰብ ይቀናናል። በጎሣ መደራጀት በራሱ ችግር ላይሆን ይችላል። ሆኖም ግን ኢትዮጵያዊነትን ያላስቀደመ ከሆነ ብሔራዊ ስሜትን አደጋ ላይ ይጥላል የሚል እምነት አለኝ።

ኢትዮጵያ የጋራ ቤታችን ናት። ማንም የበላይ ወይንም የበታች ሊሆንባት አይችልም። ሁላችንም እኩል ነን። ቀደምት ችግሮች ቢኖሩም ተነጋግረን መተማመንና መፍታት እንችላለን። በምንም መልኩ ቢመዘን ወደማይታረቅ ቅራኔ ዉስጥ ሊከተን የሚችል ጉዳይ አይኖርም።

ትልቅ ታሪክና ባሕል አለን። ከአፍሪካ ብቸኛ የጽሑፍ ቋንቋ ያለን ሕዝቦች ነን። ከቀደምት ስልጣኔ ዉስጥም እንመደባለን። የአክሱም ሐዉልት፣ የላሊበላ ዉቅር ቤተ ክርስቲያን፣ የፋሲል ግንብ ... ወዘተ ልንኮራባቸዉና ዐለምን ልናስደንቅ የምንችልባቸዉ ቅርሶቻችን ናቸዉ። ከሰማንያ ብሔረሰብ በላይ ያላት ሀገር እንደመሆኗ መጠን ለዐይን የሚስብ፣ ለጆሮ የሚጥምና ቀልብን ለሚገዛ የባሕል እሴቶች ባለቤት አድርጎናል።

እስኪ እናስተዉል! ሁለነገራችን'ኮ ከአፍሪካኖች ብቻ ሳይሆን ከሌላዉም ዐለም ለየት የሚያደርገን ሕዝቦች ነን። አመጋገባችን፣ የቀንና የሰዓት አቆጣጠራችን፣ ጭፈራችን፣ ደስታና ሐዘናችንን የምንገልጽበት መንገድና የምናደርገዉ ትብብር ... ስንቱን ቆጥረን እንጨርሰዋለን። የገንዘብና የመድን መሰል ተቋማት ባልዳበረበት ወቅት ሀገር በቀል የሆኑት ዕቁብና ዕድር ለዘመናት ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ሲቀርፉ እንደነበርም የሚዘነጋ አይደለም። ምንም እንኳን መንግሥት ማኅበራዊ እሴቶቻችንን ማፈራረስ ዐላማዉ በመሆኑ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እጁን በዕድሮች ላይ በማስገባቱ የቀድሞ ይዘታቸዉን እንዳጡ ቢነገርም ሕልዉናቸዉ ግን አሁንም እንደቀጠለ ነዉ።

ዐለም ያስደነቀ የጀግንነት ታሪክ ያለን ሕዝቦች ነን። የአፍሪካ፣ የላቲን አሜሪካና የእስያ አገራት በቅኝ ግዛት ሥር ሲወድቁ ነጻነታችንን ጠብቀን የኖርነዉ እኛ ብቻ ነን። የዉጭ ወራሪ ኃይሎችን መክተዉ በመጣል አባቶቻችን የከፈሉት መስዋዕት ከእኛ ዐልፎ ለአፍሪካም መመኪያ ሆኗል። ዛሬ በጥቁርነታችን ዝቅ ያለ ግምት ለሚያሳድሩ ወገኖች ኮራ ብለን ስለማንነታችን እንድንናገር ያደረጉን ትናንትና አባቶቻችን አጥንታቸዉን ከስክሰዉና ደማቸዉን አፍስሰዉ የከፈሉት መስዋዕት ነዉ። መሪዎቻችንም ሲያዋጉ የነበሩት በቤተ መንግሥት ተንደላቀዉ በመቀመጥ ጦር ብቻ በመላክ አልነበረም። እንደ አንድ ወታደር ሲዋደቁ ነበር። አፄ ዮሐንስ ከደርቡሾች ጋር ሲዋጉ ነዉ የሞቱት። ዳግማዊ አፄ ምኒሊክ ከነባለቤታቸዉ አድዋ ላይ እንዲሁም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማይጨዉ ላይ ዘምተዋል።

አባቶቻችን ኢትዮጵያን ለማቆየት ያደረጉት ተጋድሎ "መክተዉ ወይም ተዋግተዉ አሸነፉ" በሚል በዐጭሩ የሚደመደም አይደለም። የዕለት ተዕለት የዉጊያ ዉሏቸዉ ልብ የሚነካና ለዛሬ ማንነታችን ምን ያህል መስዋዕት እንደተከፈለን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነዉ። ያም ባለዉለታ ያደርገናል። ያኔ ነዉ ኢትዮጵያዊነት የዋዛ አለመሆኑ የሚገባን። ያኔ ነዉ የትኛዉም የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ ወይም ማኅበራዊ ችግሮች ኢትዮጵያዊነትን ጥሰዉ ለማለፍ እንደማይችሉ እርግጠኛ የምንሆነዉ።

መንግሥት በሚከተለዉ የፖለቲካ አቅጣጫ በሕዝብ መካከል መከፋፈል እንዲኖር፣ አገራዊ የሆነ ስሜት እንዲጠፋ፣ ጎሣዊ አስተሳሰብ እንዲዳብር፣ በታሪካችን እንዳንኮራ ... የሚያደርጉ ነገሮች እየተበራከቱ መጥተዋል። በዚህም ምክንያት እንደማርከሻ (Antidote) እንዲያገለግል ኢትዮጵያዊነትን የሚያጎለብት ጽሑፍ ለመጻፍ ከተነሣሣሁ ቆየሁ። ሆኖም ግን ምን ልጽፍ እችላለሁ በሚል በሐሳብ ስናወጣ ቆይቼ ነበር። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለሁ "የሃበሻ ጀብዱ" እና "የተደበቀዉ ማስታወሻ" የተሰኙ መጽሐፍት በንጽጽር የሚቀርቡበት የሥነ ጽሑፍ ክበብ ላይ የመገኘት ዕድል ገጠመኝ። በጣም ደስ የሚል አጋጣሚ ነበር። ከሁሉም በላይ ሁለቱንም መጽሐፍት ከዚያዉ በዉሰት ለማግኘት በመቻሌ ይህንን ጽሑፍ ለማዘጋጀት በቃሁ።

እነዚህን መጻሕፍት የሚያመሳስላቸዉ በርካታ ነገሮች አሉ። በቅድሚያ አማርኛ መስማትና መናገር በሚችሉ በዉጭ ሀገር ሰዎች የተጻፉ ናቸዉ። ሁለቱም የሚያወሱት ጣልያን እ.ኤ.አ. 1935 ዓ.ም. (በ1928 ዓ.ም.) በሰሜን በኩል ሀገራችንን በወረረችበት ጊዜ በሕዝባችን ላይ ስለደረሰበት ጥቃትና ለመከላከል የተደረገዉን ተጋድሎ ነዉ። ሁለቱም ጸሐፊዎች በቦታዉ ላይ ነበሩ። እንዲሁም ሁለቱም ለተመደቡበት የሠራዊት አዛዦች ልዩ ፍቅርና አክብሮት ነበራቸዉ።

"የሃበሻ ጀብዱ" የተባለዉ መጽሐፍ የቀድሞዉ ቼኮዝላቫኪያ ተወላጅ የነበሩት አዶልፍ ፓርለሳክ እ.ኤ.አ. በ1948 ዓ.ም. ተጽፎ በተጫነ ጀብሬ መኮንን የተተረጎመ ነዉ። ሚ/ር አዶልፍ ፓርለሳክ ገና በ14 አመታቸዉ ጀምሮ አገራትን የመጎብኘት ከፍተኛ ፍቅር ያደረባቸዉ ግለሰብ ነበሩ። በዚህም ምክንያት የአዉሮፓ፣ የባልካን፣ የአረብና የአፍሪካ አገራትን እንዲሁም ሶርያ፣ ፍልስጤም፣ ግብፅና ሌሎችንም አገራትን ጎብኝተዋል። በመጨረሻም ከግብፅ የአባይን ወንዝ በመከተል በሱዳን በኩል አድርገዉ ወደ ኢትዮጵያ ገብተዉ ነበር። እ.ኤ.አ, በ1935 ዓ.ም. ጣልያን ሀገራችንን በወረረበት ወቅት እንደገና ተመልሰዉ በንጉሠ ነገሥቱ የካፒቴን ማዕረግ ተሰጥቷቸዉ የሰሜን ጦር ጠቅላይ አዛዥ ወደነበሩት ራስ ካሣ ኃይሉ ዘንድ በጦር አማካሪነት ተላኩ። እዚያ በቆዩበት ጊዜ በዐይናቸዉ ያዩትን የኢትዮጵያዊነት ወኔ፣ ጀግንነትና የሀገር ፍቅር የሚተርክ "Habešská Odyssea" በሚል ርዕስ አንድ መጽሐፍ ለማሳተም በቁ። ይህ መጽሐፍ ነበር "የሃበሻ ጀብዱ" በሚል የተተረጎመዉ።

"የተደበቀዉ ማስታወሻ" በስዊዲናዊዉ ዶክተር ሀራልድ ናይስተርም ተጽፎ በዶክተር ገበየሁ ተፈሪና በደሳለኝ አለሙ በ2007 ዓ.ም. ወደ አማርኛ የተተረጎመ መጽሐፍ ነዉ። ዶክተሩ መጽሐፉን ያሳተሙት እ.ኤ.አ. 1938 ዓ.ም. በስዊዲን ቋንቋ ነበር።

ደራሲዉ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ጦርነቱ አካባቢ ዳባት ወደሚባል ቦታ ያመሩት ደጃዝማች አያሌዉ ብሩ ስለቆሰሉ እንዲያክሟቸው በተጠየቁት መሠረት ነበር። ሆኖም ግን ተግባራቸዉን እንደጨረሱ እንዳሰቡት ወዲያዉኑ የመመለስ ዕድል አላገኙም። እንደዉም እዚያዉ ከኢትዮጵያ ጦር ጋር በመንቀሳቀስ አስደናቂዉን የኢትዮጵያኖችን ጀግንነት ለማየት በቅተዋል። ጦሩን በመከተል ያዩትን የኢትዮጵያንን ተጋድሎ፣ ጦሩ በወቅቱ ሕክምናን ጨምሮ የነበረበትን አጠቃላይ ችግር እንዲሁም ሥቃይ ሳይበግረዉ ያስመዘገባቸዉ ድሎች በዝርዝር አስፍረዋል። ከብዙ በጥቂቱ በባላምባራስ ተሰማ ታንክ ላይ ዘለዉ በመዉጣት በሩን በመክፈት ወደዉስጥ ተኩሰዉ ሹፌሩን ገድለዉ ታንኩን እንዴት እንዳቃጠሉት ማንበብ የሚያስደንቅ ነዉ። ከዚያም በኋላ በተመሳሳይ ሁኔታ በርካታ ታንኮችን ጀግኖች ኢትዮጵያኖች ከጥቅም ዉጭ እንዳደረጓቸዉ እናነባለን። የጣልያኖችን መኪኖች ሳይቀር ብትንትናቸዉን እንዳወጧቸዉ ጭምር መገንዘብ ይቻላል። እንዲሁም የጦር አዝማች የነበሩት የፊታዉራሪ ሽፈራዉ ንስሐ አባት ሳይቀሩ በፈቃደኝነት በጦርነት ላይ መሳተፋቸዉ በወገናችን ዘንድ ምን ያህል የሀገር ፍቅር ስሜት ተቀጣጥሎ እንደነበር በግልጽ ያመላክታል።

ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ሁለቱም መጻሕፍት ተመሳሳይ ይዘት ስላላቸዉ የሚደጋገፉ ናቸዉ። ሆኖም ግን ለዚህ ጽሑፍ እንዲያመቸኝ ለማጣቀሻነት የተጠቀምኩት ከሃበሻ ጀብዱ ላይ ይሆናል። አንባቢዎች ግን ሁለቱንም መጽሐፍት እንዲያነቡዋቸዉ በከፍተኛ አክብሮት እጠይቃለሁ።

## 1) <u>የአባቶቻችን ተጋድሎ</u>

ጀግኖች አባቶቻችን ከጣልያን ጋር ዉጊያ የገጠሙት እጅግ ኋላ ቀር መሣሪያ አንግበዉ፣ ከተወሰኑ መደበኛ ጦር አባላት በስተቀር በቂ ወታደራዊ ሥልጠና ሳይኖራቸዉ ነበር። የረባ የሬዲዮ መገናኛ፣ ምሽግ ቆፍሮ ከአዉሮፕላን የቦንብ ዉርጅብኝ ራሳቸዉን የሚከላከሉበት ዐቅም አልነበራቸዉም። ሠራዊቱ በድካምና በዉሀ ጥም እየተሠቃየ፣ ለቀናት ዕንቅልፍ ባይኑ ሳይዞር ተራራ ወጥቶ፣ ቁልቁለት ወርዶ፣ ገደል ቧጥጦ በወኔና በሀገር ፍቅር ብቻ ተሞልቶ ያንን ከባድ ጦርነት አድርጓል።

በቂ ሥንቅና መሣሪያ አልነበራቸዉም። የጣልያን ወታደሮች ግን በገፍ ዘመናዊ መሣሪያ እስከአፍንጫዉ ድረስ መታጠቃቸዉ ሳያንስ በታንክና በአዉሮፕላን የታገዙ ነበር። የኛ ሠራዊት የያዘዉ መሣሪያ ኋላቀር መሆኑ ሳያንስ አንድ መሣሪያ ለአንድ ወታደር ማዳረስ የማይቻልበት ሁኔታ ነበር። በዚህም የተነሣ ዱላ ብቻ በመያዝ ሌላዉ ጓዱ ሲወድቅ የእሱን መሣሪያ ይዞ ለመዋጋት የሚከተለዉ ወታደር

ቁጥር ቀላል አልነበረም። መሣሪያ የያዘዉም ቢሆን በቂ ጥይት ስለማይኖረዉ የሚተኩሰዉ በቁጠባ ነበር። ይህም ሁኔታ “አንድ የኢትዮጵያ ወታደር የሚተኩሳት ጥይት የአንድ ጣልያን ወታደር ሞት ማለት ነበረች። ኢትዮጵያዉያን ፍጹም እርግጠኛ ሆነዉ ዒላማቸዉ መምታት ካልቻለ አይተኩሱም። ለምንስ ዝም ብለዉ ይተኩሱ? የሦስት ጥይት ዋጋ አንድ ማርትሬዛ ብር በገባበት ጊዜ፣ አንድ ብር የአንድ ወታደር ደመወዝ በሆነበት ሁኔታ ...” በሚል ደራሲዉ በገጽ 145 ላይ ገልጾታል።

ጸሓፊዉ የራስ ካሣን ጦር የማሰልጠን ተግባሩን እንደጨረሰ “ ... በእንዲህ አጭር ጊዜ ዉስጥ ከየጎጆዉ የመጣዉን የሰላሙን ጊዜ ገበሬ፣ የጠላት ጊዜ ወታደሩን አስተምሮ፣ ሥነ ሥርዓት አስይዞ ወታደር ማድረግ ለሰዉ ልጅ የማይቻል ይመስል የነበረዉን ሥራ ጨርሰን ለራስ ካሣ ጦር ወታደራዊ ሠልፍ ለማሳየት ዝግጁ መሆኑን አሳወቅን ...” በማለት  በገጽ 55 አስፍሯል።

ጣልያን ዉጊያዉን የሚያካሂደዉ እጅግ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ነበር። የኢትዮጵያ ጦር ይኖራል ያሉበትን ቦታ በየቀኑ ካለርኅራኄ በአዉሮፕላን ይደበድባሉ። ሠራዊታችን ከአዉሮፕላን ጥቃት ለመዳን ዋሻና ገደልን እንደመከላከያ ይጠቀምበታል። በዚህም የተነሣ የአዉሮፕላን ድምፅ ሲሰማ ወይም ሰማይ ላይ ነጫጭ አሞራ መሰል ነገሮች ሲታዩ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ራሳቸዉን ለማዳን ሲራወጡ በምናብ ማየት ልብ የሚነካ ነዉ። በዚያ ላይ ገደሉ ወይም ዋሻዉ ሙሉ ለሙሉ ከአዉሮፕላን ጥቃት እንደማያድናቸዉ በገጽ 196 እና 205 እንደሚከተለዉ ተቀምጧል። “እነዚህ ስድስት ባለሦስት አዉሮፕላኖች ያንን ገደል እየዞሩ ሲደበድቡት ቆይተዉ በድብደባዉ የተነሣ አቧራ በሰማይ ላይ ተበትኖ ገና ሳጠራ ሌሎች ስድስት አዉሮፕላኖች መጥተዉ ይደበድቡታል። በእንዲህ ዐይነት ሁኔታ ጠዋት ፀሐይ ስትወጣ የጀመሩ ቀኑን ሙሉ ሲደበድቡት ዉለዉ ጀንበር ልትጠልቅ ትንሽ ሲቀራት ያ ዕድለቢስ ገደል ዱላዉ ሲበዛበት አልችል ብሎ እየተገነደሰ ይወርድ ጀመር። ይኸ ዕደለቢስ ምስኪን ገደል እንደዚህ ወገቡ ላይ እየተቀጨ ሲወርድ ከሥሩ የመሸጉትን፣ እንደአምላክ ያመኑትን፣ እነዚያን ምስኪን ከነነፍሳቸዉ ይቀብራቸዉ ጀመር ... አዉሮፕላኖቹ በየቀኑ በሚያርከፈክፏቸዉ ቦንቦች ከ10 እስከ 100 የሚደርሱ ዕድለቢስ ወታደሮች በምሽጋቸዉ ይቀበራሉ ... ”

የአየር ድብደባዉ ሠራዊቱ ላይ ብቻ ያነጣጠረ አልነበረም። የቀንድ ከብቶችም አልቀረላቸዉም። “ ... አዉሮፕላኖቹ ታች ሜዳዉ ላይ ይግጡ የነበሩትን ከብቶች፣ አህዮችና በቅሎዎች በቦንብ እያሳደዱ ደበደቧቸዉ ... ” በሚል በገጽ 207 ላይ ተጠቅሷል። እንዲሁም ከወታደራዊ ስልት አንጻር ምንም ዐይነት ዐደጋም ይሁን ጥቅም የሌላቸዉን ተራ መንደሮች ያላንዳች ምክንያት ከማለዳ ጀምረዉ ጀምበር እስከምትጠልቅ ድረስ ያለምንም ዕረፍት የመጨረሻዋ ድንጋይ በቦንብ ተወቅራ አመድ እስክትሆን ድረስ ለሌሎች መቀጣጫ እንዲሆን እንደሚደበድቡት በገጽ 215 ላይ ተገልጿል።

አዉሮፕላኖቹ የሚተፉት ቦምብ ብቻ አልነበረም። የመርዝ ጋዝም ያርከፈክፉ ነበር። በዚህም ሰላማዊ ነዋሪዎችም ጭምር ሰለባ ሆነዋል። “ ...  ተራ እና ሰላማዊ መንደሮች ላይ ሁሉ ሳይቀር በመርዝ ጭስ የተሞሉ በርካታ የመስተዋት ቱቦዎችን ያለ ርኅራኄ መጣሉን ቀጠለ ... በርካታ ወታደሮች ልክ እንደሰከረ ሰዉ ጥቂት ደቂቃዎች ተንገዳግደዉ ሽብርክ እያሉ እስከመጨረሻዉ ማንቀላፋት ጀመሩ። በዚህ አደገኛ የመርዝ ጭስ የተቃጠሉ፣ ምንም ዐይነት ዶክተርና መድሃኒት በሌለበት የጦር አዉድማ እየተቃጠሉ ወደማይቀየርበት ዐለም አዘገሙ ... ” በሚል በገጽ 197 ላይ ተቀምጧል።

ንጽህና ለመጠበቅ ፈጽሞ በማያመችበት ሁኔታ እንዲሁም ሕክምናና መከላከያ መድሃኒት በሌለበት ሁኔታ ተላላፊ በሽታ ቢከሰት ላያስደንቅ ይችላል። ሆኖም ግን በቦምብና በመድፍ እየጋየ ላለ ሰዉ እጅግ አሳዛኝ ነበር። ይህንንም ሁኔታ ደራሲዉ በገጽ 205 እና 210 ላይ ሲያስቀምጠዉ “ ... ወታደሮቻችን በማይታይና መምጫዉ በማይታወቅ፣ መድሃኒት በሌለዉ ጠላት፣ ተስቦ እና ወረርሽኝ በየቀኑ ወደማይቀርበት ያዘግሙ ጀመር... ከሥቃያቸዉ የሚገላግላቸዉ ወይም የሚያስታምማቸዉ ማንም ሰዉ የላቸዉም። ምንም ዐይነት የሕመም ማስታገሻ መድሃኒትም የላቸዉም ... ”  ብሏል።

## 2) <u>ክሕደት</u>

ጀግኖች አባቶቻችን ጣልያንን ዉጊያ በገጠሙበት ቦታ ሁሉ ከሌላም ኃይል ጥቃት ይሰነዘርባቸዉ ነበር። ይኸዉም ለጣልያን ላደሩና አብረዉ ተሰልፈዉ በሚዋጉ ወገኖቻችን፣ በደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ የታጠቀ ጦር፣ ከጣልያን የመሣሪያ ዕርዳታ በሚያገኙ በትግራይ ሽፍቶች እንዲሁም በራያና አዘቦ ሽፍቶች ጥቃት ይሰነዝሩባቸዉ እንደነበር በስፋት ተገልጿል። ሠራዊታችን በጀግንነት ሲዋደቅ ቆይቶ ከታንክ የሚተኮሰዉን መድፍና የመትረየሱን ጋጋት መቋቋም አቅቶት ወደኋላ ለማፈግፈግ በሚገደድበት ወቅት እነዚህ ኃይላት ከኋላና ከጎን ሲተገትጉት ማንበብ እጅግ ልብ ይነካል። እነዚህ ኃይላት የሚሰነዝሩት ጥቃት ከባድና ሠራዊታችንን መፈናፈኛ የሚያሳጣ ከመሆኑም በላይ የማሸነፍ ዕድል እያለን ለሽንፈት የተዳረግንበት ሁኔታም ተከስቷል። ለዚህም ማይጨዉ ላይ የተደረገዉ ዉጊያ ተጠቃሽ ነዉ።

የማይጨዉ ዉጊያ ራሱን የቻለ ትልቅ ታሪክ አለዉ። ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ በወቅቱ የነበረዉን ዘመናዊ ጦር ይዘዉ ከዉጊያዉ በፊት ኮረም ገብተዉ ነበሩ። በሰሜን የነበረዉም ጦር ወደኋላ ተመልሶ ከእሳቸዉ ጦር ጋር ተቀላቅሎ ነበር። ማይጨዉ በጣልያን ተይዛ ነበር። የጣልያን ከፍተኛ ኃይል በዚያ ነበር። በዚያ ላይ የኛ ጦር እንዴትና መቼ ጥቃቱን እንደሚጀምር ጣልያኖች መረጃ ደርሷቸዉ ነበር። ይህም ሊሆን የቻለዉ ንጉሡ ለራስ እምሩ በቴሌግራም መልዕክት አስተላለፈዉ ነበር። ሆኖም ግን ቴሌግራሙን እንዲያደርስ የተላከዉ ፈረሰኛ በደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰዎች ተያዘ። ምንም እንኳን እነዚህ ሰዎች ደብዳቤዉን ለጣሊያኖች ለማድረስ ሲጣደፉ የአቢቹ ጦር ደርሶ ክፉኛ ቢመታቸዉም ያቺ ደብዳቤ ግን ከጣልያኖች እጅ ከመዉደቅ አልዳነችም (ገጽ 291-292 ይመለከቷል።) በዚህና በሌሎች በተጠለፉ የቴሌግራምና የሬዲዮ መልዕክቶች ሳቢያ ማርሻል ባዶሊዮ የማይጨዉን የማጥቃት ዘመቻ አስቀድሞ እንዲያዉቅና እንዲዘጋጅ ዕድል ሰጥቶታል።

ለማይጨዉ ዉጊያ የኛ ጦር የተሰለፈዉ በሦስት ራሶች መሪነት ነበር። ይኸዉም በራስ ካሣ ኃይሉ፣ በራስ ሥዩም መንገሻና በራስ ጌታቸዉ አባተ ነበር። በሦስት ረድፍ ሆነዉ ማይጨዉን ለመያዝ ከፍተኛ ርብርብ ተደረገ። በአንድ በኩል ዘመናዊ መሣሪያ እስከአፍንጫዉ ድረስ በታጠቀዉ፣ በቁጥር ከኛ ሠራዊት የሚበልጥ፣ በተዋጊ አዉሮፕላን በሚደገፍ እንዲሁም አስቀድሞ ምሽግ በያዘ ጦርና በሌላም በኩል እጅግ ኋላ ቀር መሣሪያ በያዘ ሆኖም ግን በወኔና በፍጹም ጀግንነት በተቀጣጠለ ጦር መካከል የሚደረግ በመሆኑ እጅግ ብዙ መስዋዕት ተከፍሎበታል። በዚህም መሠረት የመድፉና የቦምቡ ጥቃት የወገን ጦር ወደፊት እንዳይገፋ ስላደረገዉ ወደ ኋላ ለመለስ ተገደደ።

ግን በዚያዉ አልቀሩም። ሦስቱ ራሶች እንደገና ባደረጉት የማጥቃት እርምጃ የጣልያንን ዋና ምሽግ ሰብረዉ ለመግባት በቁ። በዚያች ቅጽበት ዳግም አድዋ ሊደገም የሰዓታት ልዩነት ቀርቶት እንደነበር በገጽ 294 ላይ ተገልጿል። ሆኖም ግን ያ ሳይሆን በፊት የራያና አዘቦ ሽፍቶች ድልን በእጁ ሊያስገባ የተቃረበዉን ወንድማቸዉን ከጀርባዉ በመጨፍጨፋቸዉ ድሉ ከእጃችን አመለጠ። ደራሲዉ ይህንን ሁኔታ “ .. ዛሬ እነዚህ ከሀዲዎች ጦርነቱን ወስነዋል። ታሪክም ሠርተዋል። ታሪኩ ግን የከሕደት ታሪክ ነዉ። ለሠላሳ ሽልንግና ለአዲስ የጣልያን መሣሪያ ሲሉ ለጣልያን ባንዳነት አድረዉ የገዛ ወንድማቸዉን ከደዉታል። ... ተሸንፈናል። ኢትዮጵያዉያን በማይጨዉ ጦርነት ተሸነፉና በየአቅጣቸዉ ወደትዉልድ መንደራቸዉ መሸሽ ጀመሩ” በማለት ቁጨቱን በዚያዉ ገጽ ላይ ገልጾታል። እንዲሁም ጃንሆይ ለእቴጌ መነን ባስተላለፉት ቴሌግራም “የኛ ጀግኖቹና ታማኞቹ ወታደሮች በማይጨዉ የጦር አዉድማ ወድቀዋል። ጀግኖቹን የመቅበሪያ ጊዜ አልነበረንም። የተረፉትም በአብዛኛዉ ቆስለዋል” ስለማለታቸዉ በገጽ 309 ላይ ተጠቅሷል።

የደራሲዉ ፈርስ አንገቱን ተመትቶ ሲወድቅ ደራሲዉ ከኮርቻዉ ላይ ተስፈንጥሮ ወድቆ ነበር። በዚያን ሰዓት እነዚያ ከሀዲዎች ገፍተዉ እየመጡ ስለነበር እንዴት ከሞት እንዳመለጠ በገጽ 295 ላይ ሲገልጽ “ ... ራሴን ስቼ ... አለቀልኝ እያልኩ ለመነሣትና ለመሮጥ ስጣጣር እስከዛሬ ድረስ ማንነታቸዉን የማላዉቀዉ ሁለት የአቢቹ ፈረሰኛ ጦሮች ጎን ለጎን ሽምጥ ጋልበዉ መጥተዉ ማጅራቴን ጨምድደዉ እየጎተቱ ወስደዉ ከአስተማማኝ ቦታ ጣሉኝ። ብዙም ሳልቆይ በዋናዉ የጦር ሰፈር ራሴን አገኘሁት” ብሏል።

ለማንኛዉም ከማይጨዉ ሽንፈት በኋላ የጣልያን ጦር ካለብዙ ዉጣ ዉረድ አዲስ አበባ ሰተት ብሎ ገባ። በነገራችን ላይ ንጉሡም ከእጅግ እልህ አስጨራሽ ጉዞ በኋላ ፍቼ ደርሱ። ከዚያም ከአዲስ አበባ በመጡ በርካታ ተሸከርካሪዎች ታጅበዉ አዲስ አበባ ገቡ። ከመለያየታቸዉ በፊት ግን ደራሲዉንና ሌሎች ፈረንጆችን ስለከፈሉት ዋጋ አመስግነዉ ስላሰናበቷቸዉ የደራሲዉ ግዳጅ እዚያዉ ፍቼ ላይ ተጠናቀቀ (ገጽ 314-315 ይመለከቷል።)

በርግጥ አንዳንዶች ለጣልያን ቢያድሩም አጋጣሚ ሲያገኙ የኢትዮጵያን ሠራዊት መርዳታቸዉ አልቀረም። እንደዉም በአንድ አጋጣሚ ደራሲዉና የተወሰኑ የጦር አባላት አንድ መንደር ገብተዉ የራስ ካሣን ጦር በመፈለግ ላይ ሳሉ ለጣልያን ያደረች አንድ መንደር ላይ ይወድቃሉ። ሆኖም ግን መንገድ እንዲመሯቸዉ ሲጠይቋቸዉ በቅንነት ረዷቸዉ። ደራሲዉ ይህንን ሁኔታ ሲገልጽ “ ... የዚች መንደር ሹም ለጣልያኖች በፍቃዱ ያደረ ቢሆንም፣ የጠላት ጦር ሳያገኘን የምንጓዝበትን መንገድ መራን ... ለጣልያን ቢያድርም ኢትዮጵያዊነቱን አልረሳም። ጥሩ መንገድ ነበር ያሳየን” በማለት በገጽ 262-263 ምስክርነቱን ሰጥቷል።

ከሁሉም በላይ ያስደነቀኝ ከጣልያን ጋር በወታደርነት ተሰልፈዉ የነበሩ ኤርትራዉያን ናቸዉ። በወቅቱ ኤርትራ በጣልያን ቅኝ ግዛት ሥር ነበረች። በመሆኑም ኤርትራዉያን በጣልያን ጦር ዉስጥ በወታደርነት ያገለግሉ ነበር። ሆኖም ግን እነዚህ ኤርትራዉያን ልባቸዉ የነበረዉ ወደእናት አገራቸዉ በመሆኑ እየከዱ ይቀላቀሉ ነበር። ይህም ሁኔታ በገጽ 138 “ ... በየቀኑ በቡድን በቡድን እየሆኑ የኤርትራ ተወላጅ የገበሬ ወታደሮች ይጎርፋሉ። እነዚህ ወታደሮች በሰላሙ ጊዜ ኤርትራ ዉስጥ ዉትድርና ገብተዉ ዛሬ ጦርነት ሲጀመር የጣልያንን ጦር እየከዱ ከነትጥቃቸዉ በምኒሊክ እየማሉ ከወንድሞቻቸዉ ጋር ይቀላቀላሉ። እነዚህ ዉድ የኤርትራ ልጆች የኢትዮጵያ ጦር በሚቀጥሉት አምስት ወራት ከጠላት ጋር ገጥሞ በመታባቸዉ የጦር አዉድማዎች ሁሉ ተሳትፈዉ ጀግንነታቸዉን አስመስክረዋል። የጣልያን ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ የጦር መኮንኖች በዉጊያ ላይ በመጀመሪያዉ ዕረድፍ ኤርትራዉያንን አሰልፎ አስተማማኝ በሆነ ርቀት ይከተሉ ነበር። ኤርትራዉያን ታዲያ ሁሌም ከኢትዮጵያዊዉ ጦር ጋር በገጠሙ ጊዜ ወይ ፈጽሞ አይተኩሱም፣ አልያም ሆን ብለዉ ወደሰማይ እየተኮሱ

ከወንድሞቻቸዉ ጋር ይቀላቀሉ ነበር። ኢትዮጵያዉያንም ኤርትራዉያንን ትጥቅ ለማስፈታት ጊዜ ሳይፈጁ አልፈዉ የጣልያኑን ጦር ይገጥሙ ነበር … ኤርትራዉያን በሚበዙበት የጣልያን ክፍለ ጦሮች ብዙ ጊዜ ብጥብጥ ይነሣ ነበር። በአብዛኛዉ ኤርትራዉያን ጣልያናዊ አለቆቻቸዉን ረሽነዉ ከነሙሉ ትጥቃቸዉ ወደ ኢትዮጵያን ወንድሞቻቸዉ ወገን የሚገቡበት ጊዜ ትንሽ አልነበረም … ” በሚል ነበር የተቀመጠዉ።

በርግጥ ጣልያንን የከዱ በመምሰል ከእኛ ሠራዊት ጋር በመቀላቀል የኢትዮጵያን ጦር የወጉ ኤርትራዉያን እንዳሉ በገጽ 254 ላይ ተጠቅሷል። እንደዚህ ዐይነት ሁኔታ የተጠቀሰዉ ግን አንድ ቦታ ብቻ ነዉ። በአመዛኙ ግን እንደዚያ አልነበረም።

**<u>ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ</u>**




እ.ኤ.አ. ከ1907 እስከ 1985 ዓ. ም. ድረስ የኖሩት ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ የራስ አርአያሥላሴ ዮሐንስ የልጅ ልጅ ናቸዉ። ምንም እንኳን የንጉሱን ልጅ ልዕልት ዘነበወርቅ ኃይለ ሥላሴን ያገቡ ቢሆንም ልዕልቲቷ በዐጭር ጊዜ ዉስጥ ሊሞቱ በቅተዋል። ለአሚሚታቸዉም ባለቤታቸዉን ተጠያቂ ያደርጓቸዋል።

ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ጣልያን ሀገራችንን በወረረበት ጊዜ መቀሌ የነበረዉ ጦር አዛዥ የነበሩ ቢሆንም ወዲያዉኑ ለጣልያን በማደር ተባባሪነታቸዉን በገሐድ አወጁ። ጣልያኖችም የጦር መማክርቱ ከሰሜኑ ግንባር አዛዥ ከነበረዉ ጄኔራል ደ ቦኖ ጋር ሆነዉ የተነሡትን ፎቶ ግራፍ በተነዉ። በዚህ የተቆጡ የትግራይ አርበኞች ቤታቸዉን አቃጥለዉታል። አንዳንድ ምንጮች እንደሚጠቁሙት ደጃዝማቹና የእሱ ተባባሪዎች የጣልያን ወረራ እንዲሳካ ንቁ ተሳትፎ እንደነበራቸዉ ይነገራል። የሆነዉ ሆኖ ደጃዝማቹ ለጣልያኖች ሙሉ ለሙሉ ታማኝ በመሆን ዘልቀዋል። ለዚህ ዉለታቸዉም ጣልያኖች በርካታ የጦር መሣሪያና ገንዘብ ሰጥተዋቸዋል። እንዲሁም “ራስ” የሚል ማዕረግ ሰጥተዋቸዉ የነበረ ቢሆንም በስተኋላ አፄ ኃይለ ሥላሴ ይህንን ማዕረግ በመግፈፍ ወደ ቀድሞ ደጃዝማችነታቸዉ መልሰዋቸዋል።

በሰሜኑ ጦርነት ጊዜ ከተከታዮቻቸዉ ጋር የኢትዮጵያን ጦር እግር በእግር እየተከተሉ በያዙት ዘመናዊ መሣሪያ ሲያጠቁ የነበሩት ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ በዐምስቱ ዓመት የአርበኝነት ጊዜ ጀግኖቻችን በዱር በገደሉ ሲዋደቁ እሳቸዉ ግን እ.ኤ.አ. በግንቦት 1938 ዓ.ም. የጀርመኑ አዶልፍ ሂትለር ጣልያንን ይጎበኝ ስለነበር “እንኳን ደህና መጣህ” ለማለት በሮም ተገኝተዉ ነበር።

የእንግሊዝ ጦር ሀገራችን በገባ ጊዜ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከጣልያኖች ጋር ሲጻጻፉ ስላገኟቸዉ በቁጥጥር ሥር በማዋል በወቅቱ ያስተዳድሩት ወደነበረዉ አስመራ ወሰዷቸዉ። አፄ ኃይለ ሥላሴ ከስደት እንደተመለሱ ደጃዝማቹ የሠሩትን የሀገር ክሕደት ወንጀል በማተት አሳልፎ እንዲሰጣቸዉ ጠይቀዉ ነበር። የእንግሊዝ መንግሥት ግን ከግድያ ባነሰ ቅጣት እንደሚቀጡ ማስተማመኛ ካገኘ አሳልፎ እንደሚሰጣቸዉ ቃል የገባ ቢሆንም ለደኅንነታቸዉ በሚል ወደ ሲሸልስ ወሰዳቸዉ።

ተላልፈዉ እንዲሰጡ የሚቀርበዉ ጥያቄ ስለቀጠለ እ.ኤ.አ. 1946 ዓ.ም. ለኢትዮጵያ መንግሥት ተላልፈዉ ተሰጡ። በቀጣይ ዓመትም ጉዳያቸዉ ታይቶ “የፋሽስት ተባባሪና ሀገር ከዳተኛ” በሚል ተፈረደባቸዉ። ከዚያም ንጉሡን ምሕረት በመጠየቃቸዉ የሞት ፍርዱ ወደ ዕድሜ ልክ እስራት በመቀየሩ መጀመሪያራስ ጎሬ በመቀጠልም ወደ አምቦ ተወስደዉ እስከለዉጡ ድረስ ለሀያ ስምንት አመታት የቤት ዉስጥ እስረኛ በመሆን አሳለፉ። ደርግ ሥልጣን እንደያዘ ነጻ የወጡ ቢሆንም “የፋሽስት ተባባሪና ሀገር ከዳተኛ” ተደርገዉ መቆጠራቸዉ ግን አልቀረም ነበር። ከዚያም በላይ በገሐድ እስረኛ ናቸዉ ባይባልም እዚያዉ አምቦ ዉስጥ ከቤት እንዳይወጡ ስለተደረጉ እ.ኤ.አ 1985 ዓ.ም. እስከሞቱበት ጊዜ በዚያ ዐይነት ሁኔታ ለመቀጠል ተገደዋል።

ዛሬም ለወያኔ ያደሩ በርካታ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳዉያን አሉ። ከሥርዓቱ ጋር በመጣበቅ ስለሚያገኙት ጥቅም እንጂ ሀገራችን ወዴት እያዘመመች እንደሆነ ለማሰብ ቅንጣት ታህል ፍላጎት የላቸዉም። ዛሬ በድሎት የታወረዉ ኅሊናቸዉ ነገ ለዉርደትና ለዕድሜ ልክ መሣቀቅ እንደሚመራቸዉ አያጠራጥርም።

**ራስ ጌታቸዉ አባተ**

ራስ ጌታቸዉ አባተ የሀገር ጉዳይ ሚኒስቴር የነበሩ ሲሆን እ.ኤ.አ. ወደማይጨዉ የዘመቱት የከፋን ጦር ይዘዉ ነበር። የክቡር ዘበኛ ጦርንም የመሩት እኒህ ግለሰብ ነበሩ። ምንም እንኳን ከንጉሡ ጋር ወደ ስደት ያመሩ ቢሆንም የኋላ ኋላ ከንጉሣዊ ቤተሰብ ተነጥለዉ ወደ ኢየሩሳሌም አምርተዉ በመጨረሻም ወደ ሀገር ቤት በመመለስ ለጣልያን እንዳደሩ ይነገራል። በመጨረሻም ጣልያን ከሀገራችን ከወጣ በኋላ ተይዘዉ ወደ ጅማና አርሲ በግዞት ለመላክ ተዳረጉ።

በክሕደት ላይ ስለተሰማሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ላይ ለመጻፍ የፈለግኩት አባቶቻችን ተጋድሎ ያደረጉት ፊት ለፊት ከሚታወቅ የጣልያን ጦር ብቻ እንዳልሆነና የከፈሉትን የመስዋዕት ግዝፈት ለማሳየት ነዉ። የሆነዉ ሆኖ በሽፍትነት የተደራጁት ቡድኖች ሕዝብን የማይወክሉ የግለሰቦች ስብስብ እንደሆነ መገንዘብ እንዳለብን ለመግለጽ እወዳለሁ።

## 3) ጀግኖቻችን ሲወደሱ


ራስ ካሣ ኃይሉ ዳርጌ


ራስ ሥዩም መንገሻ አምባላጌ ላይ


ራስ ሙሉጌታ ይገዙ


ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ


ደጃዝማች አያሌዉ ብሩ

3.1) **ራስ ካሣ ኃይሉ ዳርጌ**

ከዳግማዊ አፄ ምኒሊክ የሚዛመዱት ራስ ካሣ ኃይሉ ዳርጌ የተወለዱት ሰላሌ በሚባል ቦታ እ.ኤ.አ. ከAugust 7, 1881 ዓ. ም. (ነሐሴ 1 ቀን 1873 ዓ.ም.) ነበር። ከወለዷቸዉ ልጆች ዉስጥ የኤርትራ የበላይ ጠባቂ የነበሩትና ደርግ ከረሸናቸዉ የአፄ ኃይለ ሥላሴ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ዉስጥ አንዱ የሆኑት ልዑል አሥራተ ካሣ ይገኙበታል። ራስ ካሣ ኃይሉ እ.ኤ.አ. በNov. 16, 1956 ዓ. ም. (ህዳር 8 ቀን 1949 ዓ.ም.) ነበር የሞቱት።

የሰሜኑን ጦር የመሩት ራስ ካሣ ኃይሉ ዳርጌ ነበሩ። ወደ ግንባር የዘመቱት ደጃዝማች አበራና ደጃዝማች ወንድወሰን ከሚባሉ ልጆቻቸዉ ጋር ነበር። ሦስት ቀንና ሌሊት የፈጀዉን ከባዱንና የመጀመሪያዉን የተንቤን ጦርነት በመምራት ለድል አብቅተዉታል።

ራስ ካሣ ኃይሉ አዛኛና ለሕዝባቸዉ ተቆርቋሪ ነበሩ። የጣልያን አዉሮላኖች አድዋን በቦንብ እንደበደቡና የራስ ካሣ ጦር በሚቀጥለዉ ቀን ለዉጊያ ወደዚያዉ እንደሚሄዱ ባወጁበት ሰዓት የተሰማቸዉን ደራሲዉ በገጽ 58 ሲገልጽ " ... ራስ ካሣ ዕልፍኝ ገብተዉ በር ዘግተዉ ለረጅም ሰዓት ዐለቀሱ። ዕንባቸዉን ዐነቡ። የራስ ካሣ ዕንባ የፍርኀት አልነበረም። የራስ ካሣ ዕንባ ለብዙ ሺህ ያለ ሃጢአታቸዉ ለሚረግፉ የኢትዮጵያ ልጆች ነበር ..." በማለት ነበር።

### 3.2) ራስ ሥዩም መንገሻ

አፄ ዮሐንስ ሁለት ልጅ ሲኖሯቸዉ እነሱም ራስ አርአያ ሥላሴ እና ራስ መንገሻ ዮሐንስ ይባላሉ። እ.ኤ.አ. ከሰኔ 21, 1887 ዓ.ም. እስከ ታህሳስ 15 ቀን 1960 ዓ.ም. (ከሰኔ 15 ቀን 1879 እስከ ታህሳስ 6 ቀን 1953 ዓ.ም.) ድረስ የኖሩት ራስ ሥዩም መንገሻ የራስ መንገሻ ዮሐንስ ልጅ ማለትም የአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅ ናቸዉ። እንዲሁም የትግራይ አስተዳዳሪ የነበሩትና ከልዕልት አይዳ ደስታ (የልዕልት ተናኘወርቅ ልጅ) ጋር የተጋቡት የልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም አባት ናቸዉ። በተጨማሪም ሌላዋ ልጃቸዉ ወ/ሮ ወለተ እስራኤል ሥዩም የአልጋ ወራሽ አስፋወሰን ባለቤት ነበሩ።

ራስ ሥዩም መንገሻ እ.ኤ.አ ጥቅምት ከ1935 (ጥቅምት 1928) እስከ የካቲት 1936 ዓ.ም. (የካቲት 1928 ዓ.ም) ድረስ የትግራይ ጦር አዛዥ ነበሩ። በዚያ ጦርነት ላይ በቆራጥነት ጦራቸዉን መርተዉ ከጣልያን ጋር የተፋለሙ ታላቅ ጀግና ነበሩ። ሆኖም ግን በጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ በተመራዉ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በቁጥጥር ዉለዉ ከተገደሉት ዉስጥ አንዱ ነበሩ።

### 3.3) ራስ ሙሉጌታ ይገዙ

ራስ ሙሉጌታ ይገዙ የዘመቱት ከፈረንሳይ ሀገር ወታደራዊ ትምህርቱን አቋርጦ ከመጣዉ ወንድ ልጃቸዉ ጋር ነበር። በወቅቱ የጦር ሚኒስቴር የነበሩ ሲሆን ጣልያን አምባራዶን ለመያዝ ለሚያደርገዉ ዉጊያ ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረጉ ጀግና ነበሩ። ምንም እንኳን የጣልያን ጦር በቁጥርና በመሣሪያ ጥራት ቢበልጥም የአዉሮፕላን ድብደባዉና እሳት የሚተፉትን መድፎችና መትረየስ በመቋቋም በመጀመሪያ ቀን በጠላት ጦር ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዳደረሱ በገጽ 243 ላይ ተጠቅሷል። ሆኖም ግን ጣልያን በቀጣይ ቀናት ጦሩን እንደገና በማሰባሰብ የማጥቃት ሙከራ አደረገ። ያም አልተሳካም ነበር። በጨበጣ ዉጊያ ላይም ኢትዮጵያኖች አይለዉ ነበር። በዚያ ጦርነት ብቻ የጣልያን 15,000 ወታደሮች በላይ እንዳጣና ከኢትዮጵያንም በኩል ከ12,000 እስከ ሀያ ሺህ ድረስ የሚገመት ጀግኖች እንደተሰዉ በገጽ 244 ላይ ተገልጿል።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ጦር እንዴት እንዳፈገፈ መጽሐፉ ገጽ 244 ላይ ሲገልጽ "ከረፋዱ ጀምሮ ቀኑን ሙሉ ከሰማይ እንደ ነሐሴ ቦምብ ሲወርድበት፣ በምድር የመድፍና የመትረየስ ጥይት ሲቀጠቅጠዉ ለዋለዉና ላመሸዉ ጦራቸዉ ራስ ሙሉጌታ ምሽቱ ላይ ጦሩ አምባራዶምን ለቆ እንዲወጣ ትዕዛዝ ሰጡ" ይላል።

የራስ ሙሉጌታ ወታደሮች ከአዉሮፕላን እንደዶፍ ከሚወርድባቸዉ ቦንብና የጢስ መርዝ ለማምለጥ በቻሉት ፍጥነት በየጫካዉና በየጢሻዉ እየገቡ ሲበተኑ ቀድሞ መሽጎ ይጠብቃቸዉ የነበረዉ የራያና አዘቦ ሽፍታ ጣልያን ባስታጠቀዉ መሣሪያ ለቀማቸዉ፣ በጥይት ዒላማቸዉ ላይ ያልገባዉንና ደክሞት በየዛፉ ጥላ ሥር ያንቀላፋዉን ወታደር ደግሞ በጩቤ ከኋላዉ እየወጉ ገድለዉ እንደዘረፏቸዉ በገጽ 245 ላይ ተጠቅሷል።

በዚህ ዉጊያ ላይ እንደማንም ተራ ባላገር ወታደር ሁሉ በታላቅ ጀግንነት ከነልጃቸዉ የተሳተፉት ራስ ሙሉጌታ ይገዙ የአሸንጌን ወንዝ በመሻገር ላይ እያሉ የምስኪን ወታደሮቻቸዉ ዕጣ ገጠማቸዉ። ደራሲዉ ይህን ሁኔታ በገጽ 246 ላይ ልብ በሚነካ ሁኔታ ሲገልጸዉ "ይህንን ሁሉ መከራና ፍዳ ተወጥተዉ፣ ሠራዊታቸዉን በታላቅ ጀግንነት መርተዉ ከጠላት ጋር ተፋጠዉ እንዳልተዋጉ ሁሉ ... ከልጃቸዉ ጋር የአሸንጌን ወንዝ በፈረስ በመሻገር ላይ እንዳሉ ታልመዉ በተተኮሱ ሁለት የራያና አዘቦ ሽፍቶች ተመትተዉ ወደቁ ... አባቱን ለመርዳት ከፈረሱ ላይ በመዉረድ አባቱን ለመደገፍ ጎንበስ ያለዉንም ልቻቸዉን ታልመዉ ተደጋግመዉ የተተኮሱ ጥይቶች በአባቱ ሬሳ ላይ ጣሉት" በማለት ነበር። ራስ ሙሉጌታ የተገደሉት እ.ኤ.አ. በFeb. 27, 1936 ዓ.ም. (የካቲት 19 ቀን 1928 ዓ.ም.) ነበር።

### 3.4) ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ

ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ እ.ኤ.አ. Nov. 23, 1892 (ሕዳር 15 ቀን 1885 ዓ.ም. ) እስከ Aug. 15 1980 (ነሐሴ 9 ቀን 1972 ዓ.ም.) የኖሩ አርበኛና ዲፕሎማት ነበሩ። ልጃቸዉ ልጅ ሚካኤል እምሩን ጨምሮ በወቅቱ ተራማጅ አስተሳሰብ እንዳላቸዉ የሚነገርላቸዉ ራስ እምሩ አገራቸዉን በበርካታ ኃላፊነት ቦታ አገልግለዋል። በሰሜን በተደረገዉ ዉጊያ ትልቅ ድርሻ የነበራቸዉ ሲሆን ከዚያም በኋላ ጣልያን ከሀገራችን እስከሚወጣበት ጊዜ ድረስ በዱር በገደል የተዋደቁ አርበኛ ነበሩ።

### 3.5) <u>ደጃዝማች አያሌዉ ብሩ</u>

ደጃዝማች አያሌዉ ብሩ የኖሩት እ.ኤ.አ. ከ1892 እስከ ግንቦት 1945 ነበር። ለአቴጌ ጣይቱና ለአፄ ኃይለ ሥላሴ እንደሚዛመዱ የሚነገርላቸዉ ደጃዝማች አያሌዉ ብሩ ያገቡት የራስ ካሣ ኃይሉ ዳርጌን ሁለተኛ ልጅ ነበር።
አገራቸዉን በተለያየ ኃላፊነት የአገለገሉና በሰሜኑ ጦርነት ላይ በበርካታ የዉጊያ ወረዳ ላይ የተካፈሉ ጀግና ነበሩ። የጠላትን ጦር የመከተ የአመራር ብቃታቸዉን ያሳዩት ደጃዝማች አያሌዉ ለጦር ምርኮኞች የሚያሳዩት ርኅራኄ የሚደነቅ ነበር። እኒህ ጀግና ከራስ እምሩ ጦር ጋር በመቀናጀት በርካታ ተጋድሎ አድርገዋል።

### 3.6) <u>ወጣቱ አቢቹ</u>

በደጃዝማች አበራ የሚመራዉ ጦር ጋር ከሰላሌ የመጣዉ አቢቹ በወቅቱ ዕድሜዉ 16 ወይም 17 ቢሆን ነበር። አባቱ አዲስ አበባ ልከዉ ያስተማሩት አቢቹ በሚቀጥለዉ ዓመት ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ፈረንሳይ ሊሄድ የነበረ ቢሆንም ሀገር በመወረሯ ምክንያት ከሁለት ታላላቅ ወንድሞቹ ጋር ሊዘምት ቻለ። ወንድሞቹ በፊታዉራሪ ማዕረግ የወረጃርሶ ጦር መሪዎች ነበሩ። የአቢቹ ሕይወት የተቀየረዉ በተንቤን ዉጊያ ላይ በአንድ ቀን ሁለቱንም ወንድሞቹን በማጣቱ ነበር። የአንደኛዉ ወንድሙ አስከሬን በወቅቱ አልተገኘም ነበር። የሌላዉ ወንድሙን አስከሬን ግን ከዋርካ ሥር ቀብሮታል።

አቢቹ ወንድሞቹን ተከቶ የወረጃርሶ ፊታዉራሪ በመሆን ጦሩን መምራት ይጠበቅበት ነበር። ሆኖም ግን ወንድሞቹን በማጣቱ ልቡ ስለተነካ ከአንድ ቋጥኝ ላይ ሳይነሣ ሁለተኛ ቀን እንዳሳለፈ በገጽ 184 ላይ ተገልጿል።

አስከሬኑ ያልተገኘዉ አንደኛዉ ወንድሙ በጣልያኖች ተማርኮ እንደሚሠቃይ እምነት ነበረዉ። በዚህም የተነሣ ወንድሙን ነጻ ለማዉጣት ከጥቂት ወታደሮች ጋር ንጋት ላይ የጦር ሠፈሩን ለቅቆ እንደሚሄድ ለደጃዝማች አበራ አስታወቀ። እንዳለዉም ሊነጋጋ ሲል 200 የሚሆኑ ወታደሮችን እየመራ ከጦር ሠፈሩ ወጣ።

መጀመሪያ አካባቢ የደረሰበት ባለመታወቁ የተለያዩ ጥርጣሬዎች የተፈጠረ ቢሆንም እያደር ግን በርካታ ጀብዱዎች መፈጸሙ መወራት ጀመረ። በሌላም በኩል ተማርኳል ወይም የመድፍ ጥይት በጣጥሶ ጥሎታል ተብሎ የተገመተዉ ወንድሙ ለካንስ ቆስሎ የነበረ ሲሆን አገግሞ ጦሩን መምራት ጀመረ። ሆኖም ግን አቢቹ ወደእናት ጦሩ ሳይቀላቀል ቀረ። እንደዉም ቀስ በቀስ በርካታ ወጣት ተዋጊዎች ዋና ጦራቸዉን በመተዉ ከአቢቹ ጦር ጋር መቀላቀል ጀመሩ። ወደ እናት ጦሩ እንዲቀላቀል ወንድሙ መልዕክተኞች ቢልክም ግማሾቹ በዚያዉ ቀሩ።

አቢቹ መጀመሪያ ላይ አነስተኛ የተበተኑ የጣልያን ጦር ላይ በደረቅ ሌሊት ዐደጋ በመጣል፣ ሥንቅና ትጥቅ በመዝረፍ ጦሩን በዘመናዊ መሣሪያ አስታጠቀ። ዐልፎ ዐልፎም በሌሊት የጣልያኖችን የጦር ሠፈር ሰብሮ በመግባት ዐደጋ በመጣል ንብረት ይዘርፍ ነበር። ታዲያ ከሚዘርፋቸዉ ንብረቶች ዉስጥ የተረፈዉንና የማይፈልጋቸዉን ወደ ዋናዉ ጦር ይልክ ነበር (ገጽ 188 ይመለከቷል።)

በሌላም በኩል ድርጊቱ ያስቆጣቸዉ የጣልያን ጦር የበላይ አዛዦች የአቢቹን ጦር አሳደዉ እንዲሙቱላቸዉ ለትግራይ ሽፍቶች ከፍተኛ ገንዘብና መሣሪያ ለገሡ። ሆኖም ግን ሽፍቶቹ የአቢቹን ጦር በመፈለግ ላይ ሳሉ ማርሻል ባዳሊዮ በቅርቡ ከሮማ ከተላከለት ትኩስ ጦር ላይ ሁለት ሻለቃ ጦር ቀንሶ በዘመናዉ ጦር አስታጥቆ ወደተንቤን የላከዉን ጦር ሲያዘግም አቢቹ ተመለከተ። ከዚያም ጦሩ ምሽቱን ያልፍበታል ብሎ የገመተዉ ቦታ ላይ ከራሳቸዉ ከዘረፈዉ በርካታ ቤንዚን የተሞሉ ትላልቅ ቆርቆሮዎች ዉስጥ ከፊሉን በየቁጥቋጦ ዉስጥ በማፍሰስ ራቅ ብሎ መሸገ። የጣልያን ጦርም እንደተገመተዉ ድንኳናቸዉን እዚያዉ ተከለዉ ሰፈሩ።

እኩለ ሌሊት ላይ ያንን ቤንዚን የጠገበ ቁጥቋጦ እሳት ስለለቀቀበት ወታደሮቹ ግራ ገብቷቸዉ ሲደናበሩ የአቢቹ ጦር ግንባር ግንባራቸዉን በማለት አንድ በአንድ ለቀማቸዉ። እንደተለመደዉ ከዚህ ጦር የወረሳቸዉን ንብረት፣ ጦርና የምግብ ቁሳቁስ ለዋና ጦሩ አከፋፈለዉ።

ሌላ ጊዜ ደግሞ ሽፍቶች አስቸጋሪ መንገድ ላይ ጠብቀዉት አላሳልፍ በማለት በከፈቱበት ተኩስ ሁለት ተዋጊዎችን ገደሉበት። በዚህ የተናደደዉ አቢቹ ሽፍቶቹ የመሸጉበትን መንደር ሽማግሌዎች፣ ሴቶችና ሕፃናት ለቀዉ እንዲወጡ ካስደረገ በኋላ መንደሩን በእሳት አጋየዉ። ከዚያም ከመሸገበት በመዉጣት ሸሽት የጀመረዉን ሽፍታ እነአቢቹ እያሳደዱ ቀጠቀጡት (ገጽ 189 -190 ይመለከቷል።)

የተማረና ያለዕድሜዉ የበሰለ የልጅ አዋቂ እንደሆነ በሚነገርለት በአቢቹ የሚመራዉ ጦር በጣልያን ጦር ላይ ያስከተለዉ ጉዳት ይህ ብቻ አልነበረም። እጅግ ብዙና መጠነ ሰፊ ነበር። ከሁሉም በላይ በተለያየ የጦር ኃላፊዎች ሥር የነበረዉ ሠራዊታችን ዉጊያ ላይ እንዳለ የአቢቹ ጦር ድንገት ደርሶ ለጦሩ የሚያደርገዉ እገዛ ለወገን ትልቅ መከታ እንዲሁም ለጣልያኖች ትልቅ ራስ ምታት ነበር። ንጉሡም " ... ይቺ አንድ ፍሬ ደጃዝማች ከኛ በላይ ጀብዱ እየሠራች መሆኑን እንሰማለን ... " በማለት ለአቢቹ አድናቆታቸዉን ስለመግለጻቸዉ በገጽ 288 ላይ ተጠቅሷል።

ደራሲዉ ስለአቢቹ ጦር አወቃቀር በገጽ 274 ላይ ሲገልጽ "1ኛ በጄኔራል ሀብቶም የሚመራ የሀማሴን ልጆች ጦር፣ 2ኛ በጄኔራል ተስፋጽዮን የሚመራ የትግራይ (የመቀሌ) ልጆች ጦር፣ 3ኛ በጄኔራል ጋሹ የሚመራዉ የጎጃም (የዳሞት) ልጆች ጦር እና 4ኛ በጄኔራል ወርቁ የሚመራዉ ዋናዉ የሰላሌ ልጆች ጦር" በማለት ያስቀምጠዋል። እነዚህ አራት ጄኔራሎች ከነጦራቸዉ ታማኝነታቸዉ ለአቢቹ እንደሆነም ተጠቅሷል።

የማይጨዉ ዉጊያ ላይ የአቢቹ ጦር ከፍተኛ ሚና ተጫዉቷል። ሆኖም ግን እንደሌላዉ ሠራዊታችን በራያና በአዘቦዎች ጉዳት እንደደረሰበት ደራሲዉ በገጽ 316 ላይ ሲገልጽ "የአቢቹ ጦር በቀበርቶዉ ጦርነት በአዘቦዎችና በራያዎች ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰበት ሁላችንም ሰምተናል። ጃንሆይ ሳይቀሩ አሻፈረኝ ልጁን ብቻዉን ጥለን አንሄድም እስከማለት ደርሰዉ ነበር። እንደዚያም ሆኖ ጦሩ ከፍተኛ የሚባለዉን መስዋዕት ከፍሎ ከቆርበቶ እሳት ዉስጥ እንደወጣና መሪዉ አቢቹም በሕይወት እንደተረፈ ሰምተናል" በማለት ገልጿል።

ደራሲዉ ለመጨረሻ ጊዜ  አቢቹን ሰላሌ አግኝቶት ስሜታዊ በሆነ ሁኔታ እንደተሰናበተዉ ይገልጻል። በነገራችን ላይ  ደራሲዉ ለአቢቹ የተለየ ፍቅርና አክብሮት ነበረዉ። በጀግንነቱ ያደንቀዋል፤ ይኮራበታልም። እኛም ይህንን ጀግና ልንዘክረዉ ይገባል። ከዚያም በላይ ለስሙ መጠሪያ ሊሆን የሚገባ መታሰቢያ ሊሠራለት የሚገባ ጀግና እንደሆነ አምናለሁ።

## ማጠቃለያ

ቀደምት ጀግኖቻችን የሚያኮራ ተጋድሎ የፈጸሙት ሁሉም በጎሣ፣ በቀዬ፣ በሃይማኖት ... ወዘተ አንድ ሆነዉ አልነበረም። በየፈርጁ ልዩነት ቢኖርም ሁሉም ግን የአንድ ሀገር ሕዝቦች ነበሩ። በሀገር ጉዳይ የሚለያዩበት ነጥብ ባለመኖሩም ነበር የጋራ ድል ባለቤት ሊሆኑ የበቁት። ስለሆነም ዛሬ ልዩነታችንን አቻችለን የጋራ ቤታችንን ካልሠራን ለማንም የማይበጅ ዉጤን ነዉ የሚከተለዉ።

የተጋረጠብንን ዐደጋ ለማምለጥ እንደአባቶቻችን የተባበረ ክንድ ይስፈልገናል። ብንተባበር ባለድል እንሆናለን። በሚያለያዩን ነገሮች ላይ ጊዜአችንን ብናጠፋ ግን ለወያኔ ሥልጣን ማረዘሚያ መንገድ ከመክፈት ባሻገር ለማናችንም የሚጠቅም ዉጤት ማምጣት አንችልም።

ቸር ይግጠመን
የዚህን ጽሑፍ አቅራቢ ለማግኘት ለምትፈልጉ፡- mekonnen_ashagre@yahoo.com